# የአባይን ወንዝ ለመሸጥና በግድቡ ድልድይ ስራ መደራደር ሸንደፍደፍ እንዴት ብሎ? ተርጉምስ???

December 25, 2017

|

ከአስገደ ገብረስላሴ ፣
መቀለ

---

የቀይ ባህር በራችን ማሳጣታቸው ኣይበቃም ብሎዋቸው ሉኣላዊ የኣባይ ወንዛችንና የ100ሚሊዮን የኢትጱያ ህዝቦች የባለቤትነት መብት ለመቀማት ፣ ህዝቦች እድሜና ጾታ በማይለይ ከልጆቻቸው የእለት ጉርስ ቀምተው ገንዘባቸው ኣዋጥተው እየገደቡት ያሉትና የጥረታቸው ውጤት ወፍራም እንጀራ ሊጎርሱ እና ሉኣላዊ ወንዛቸው ተከብሮ እንዲኖር ለማየት እዬተመኙ ጊዜው በደረሰበት ወቅት የኣባይ ሉኣላውነት ኣሳልፈው ለመሸጥ ሽርጉድ ማለታቸው ከ100ሚሊዮን በላይ የኢትዮጱያ ህዝቦች ኣሸራቸው ያሳረፉበት እና የማይፋቀው ከመሆኑም በላይ በኣባይ ሉኣላውነት ጉዳይ ኢህኣደግ የቀይባህር ጉዳይ እንደሸወዳቸው ሁሉ ። በኣባይ የባለቤትነት መብቱ በካሃዲዎች በቀላሉ ተታልሎ እሚለቃቸው እና እሚሸወደው ይመስላችኃልን??



የኢትዮጱያ ህዝበች በቡዙ ቢሊዮን ብር የሚገመት እያወጡ የኣባይ ግድብ ወደ መጠቃለል ደረጃ ኣቃርበውች ያሉ ለህወሓት ኢህኣደግ ፓርቲና ኣጋሮቹ ፣ ስርኣታቸውን ስለሚወዳቸው ኣይደለም ዋናው ያናሳሳቸው ምክንያት ኢትዮጱያውያን ከጥንት

ጀምረው በውረድ ተዋረድ ይዘውት የመጡ ባህልና ታሪካዊ እሴት የሃገራችን ሉኣሏውነት የሚነካ በሚፈጠርበት ወቅት ለሀገራችንና ህዝቦቻ የሚበሉ ጅቦች ሲመጡባቸው በገዥዎች ፍላጎትና ሴራ በማሃከላቸው ለሚፈጥሩት ልዩነት ወደ ጎን በመተው ነበረን አለን የሚል ቂም በቀል መቃቃር ትተው ለሃገራዊ ጸጥታና ድህንነታቸው ቅድምያ በመስጠት ወይ በማየት ለባእድ ጠላቶች ኣብረው ይከላከላሉ ፤ያጠቃሉ ፣ በተለይ ደግሞ በቀይባህር ለእነቱርክ ፤ጣልያን ወዘ ተ ፤በምእራብ በነግብጾች ተደግፈው የመጡ ድርቡሾች ፣ በምስራቅ ሱሚልን እንደ ሽፋን ተጠቅመው የመጡ ወራሪ ሀይሎች ፣ በቅርቡ ጊዜ የምናስታውሰው ደግሞ የሻኣብያ ወረራና እሱን ሽፋን ኣድርገው እነግብጾችና ሌሎች ኣረብ ኣገሮች ወራሪዎች ኢትዮጲያውያን ግን ኣብረው እንደ ኣንድሰው ኣንድ ስትንፋስ ፈጥረው ተሰውተው ኣስከሬናቸው በኣንድ ምሽግ ተቃቅፈው ኣርፈዋል ። በሰላም ጊዜም ኣብረው ይኖራሉ በጋብቻ በኣካባቢ
ተሳስረው ፤ወሰን ጎጥ ሳይለያቸው ኣበረው እየኑሩ ነበር።

በመሆኑ እነዚህ ሰዎች ህዝቦች እየገነቡት የመጡ ታሪካዊ እሴታቸን ባለንበት የሰለጠነ ኣለም ወደፊት እየገሰገሰች ባለችበት 21ኛ ክፍለዘመን የኢህኣደግ እና ኣጋር ፓርቲ ፓርቲ መሪዎች ወላጆቻችን እየገነቡት የተጓዙ ወርቃዊ ታሪክ ሊጋሲያቸው ተከትለው ያረጀውን እና ዘመናውነቱ የወደቀ በመተው ለመታደስ የሚችልና እንደ መልካም እሴት የሚጠቅማችሁ ሰንቃችሁ ሀገራችንን በበለጠ ወደ የጠነከረ ዘመናዊ ኣንድነት ይዟችኃት እንደመጓዝ ፈንታ ሃገራችን በዬ ግላችሁ ፍሏጎት ለማርካት ወደ ኣልሆነ ኣቅጣጫ ልትኖዳት መፈለጋችሁ እጅጉን ያዛዝናል ።

ከላይ የዘረዘርኩዋቸው ነጥቦች ለመግለጽ የተገደድኩበት ምክንያት በኣሁኑ ጊዜ የሀገራችን ህዝቦች ቢሄር ቢሄረሰቦች በመላው ሃገራችን የሚገኙ የዩንቨርስቲ ማህበረሰብ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚገኙ ዜጎች የሚያነሱት ጥያቄዎች የገዥው ስርኣት ተገቢ መልስ እንደመስጠት ፈንታ በገዥ ፓርቲ ስር የሚገኙ የፓርቲ መሪዎች ያለፈው 27 ኣመት ጊዜ ስልጣናቸው ተጠቅመው የጥቀመኝ ልጥቀምህ እከከኝ ልከክህ በማለት የሙስናና የሃብት ወረራ ኔት ወርክ በመዘርጋት ፣ ብልሽወነታቸውና የወረሩት ሃብት ላለመጋለጥና ባገር ውስጥና በውጭ ኣገር ከመሰረታዊ የኢትዮጲያ ኣገራችን እና ህዝቦቻ ጠላቶች ሄደው ያልሰሩበት የህዝብ ሃብት መደበቅ የሄዱ መሪዎች ካሁን በፊት በዘመድ በወዳጅ በጓደኝነት የተጀራጀና የታጠቀ የጠነከረ ኔትወርክ ዘርግተው በመላው ሀገራች የሚገኙ የኮንትሮባንድ ሌቦች በመሻረክ የሀገራችን ሀብት ወረው ባገር ውስጥ የማይደበቁ ሰማይጠቀስ ህንጻዎች ውድ ቪላዎች ሰርተው ፤ባገር ውስጥ እና በውጭ የደበቁት ዶላር ፤የሰሩት እንዳይታወቅ የኢትዮጲያ ህዝቦች በዘር በሃይማኖት ፤በጎጥ በቢሄር ግጭት ፈጥረው ያጫረሱት ፤የእሮም ፤የትግራይ ፤የደቡብ የጎንደር የጎጃም ፤የጋንቤላ ፤የቤልሸንጎል ጉምዝ ፤የሱማል እናቶች በሀዘን ጥቁር ልብስ ያለበሳቸው ኣልበቃም ብሎዋቸው ። እንደገና ከመቶ ሚሊዮን በላይ የሀገራችን ህዝቦች ኣንጡራ ሃብታቸው ሰጥተው ኣሸራቸው ያሳረፉበት እና ከላይ እንደገለጽኩት ፍሬው እና ውጤቱ ለማየት በሚጓጉበት ሰኣት ወንጀላችሁ ለመደበቅ ከግብጾች ጋር ተሻርካችሁ የኣባይ ወንዝ ግደብ ለማክሸፍና ግብጾች ኣባይን ለማፍረስ ላዘጋጁት ኤፍ 16 ቦምብ ጣይ የኣመሪካ ኣውሮፕላንና ምሳይል ተከታችሁ ግድቡ ለማፍረስ የወሰናችሁና ግንኝነት እንዳላችሁ ለኢትየጲያ ህዝብ የከዳችሁ መሪዎች እንዳሏችሁ ከኢህኣደግ ስብሰባ ኣፈትልከው የወጡ መረጃዎች በማህበራዊ ሚዲያዎች እናያለን ። በተጨማሪ እነዚህ ሃገር ከሀዲዎች ኣሁንም ጉዳቸው እንዳይታወቅ በቢሄር ያተኮረ ቢሄር ከቢሄር እርስበእርሳቸው በጦርነት እንዲፋጁ በማድረግ ግጭቱ እንደ መደበቂያ ምሽግ በመጠቀም በማኸል ደረታቸው ነፍተው የቢሄራቸው የመኸር ወይፈን ሆነው ሲያንገራግሩ ይታያሉ ። ይህ ሁሉ ለመፈጸሙ ዋናዎቹ የኢህኣደግ ስራኣስፈጻሚ የፈጸመው ስህተት መሆኑ ገና ግምገማው ሳይጨርስ የሞት ንዛዜ ኣሰምታል ውጤቱ ምን ይሆን ? በእኔ እምነት ሁኔታው በሚገነዘቡት

ወገኖችም ኢህኣደግ ብቻው ገለልተኛ ቡቁ ዜጎች ከሌሉበት ብቻው እንደ የተባላሸ ወተት ቢናጥ ቢናጥ ውጤቱ ባዶ ነው ።
ለዚሁ ሁሉ ማሰረጃ ወይ ማሳያ የሚሆነን ቀደም ሲል የጎንደረ የጎጃም ህዝቦች በባኣዴን መሪዎች ተጋግለው በመነዳት እንዲሁም የህወሓት መሪዎች በፈጠሩት ንትርክ እና የዘረኝነት ፕሮፕጋንዳ እጅግ ቡዙ የትግራይ ቢሄር ተወላጆች ተገደሉ ኣካለቸው ጎደሉ በጅምላ በክረምቱ ወቅት ተሰደዱ ሀብታቸው ተወረረ ፣ተዘመተ ። የማይናቅ ወገኖችም ከጎንደርና ከጎጃም ተወላጆች ሞተዋል ። በወቅቱ የገዱና የኣባይወልዱ ቡዱኖች ኣልተነኩም ። እንዳውም ህዝቡ በቢሄር ተኮር ኣጫርሰው ሲያበቁ እንደገና ለመላው የኢትዮጲያ ህዝቦች ለመሸወድ ኣማራሩና ካድሬዎቻቸው በመቀለ እና በጎንደር የህዝብ የእርቅ ጉባኤ በሚል ስም በመስጠት ህዝቡን ሲያታልሉ ታይተዋል ። ግጭቱ ግን ኣባብሰውታል እንጅ ኣልጠፋም ።ኣሁንም ምን እንደጎደላቸው እየተጉረኑ ይታያሉ ።
በዩንፈርሲቲዎቾ ያለው ቢሄር ተኮር በትግራይ ቢሄር ያናጣጠረ ግድያ በኣዲግራት የታየው ኣጸፉ ለመመለስ ግድያ ኣናሳሽዎችና ምንጩቹ እነዚህ መሪዎች ናቸው ። በቅርብ ሳምንታት የጀመረው በሰሚል ቢሄርና በኦሮሞ ቢሄር ዘግናኝና ኣሳዛኝ የጆኖሳይድ እልቂት ጠንሳሶቹ የእሮሞ ኦሆዴድ መሪዎች ናቸው ። በኦሆዴድ ማእከላይ ኮሚቴና የክልሉ መሪዎች በኣዋጅ ኣራጋግጠውታል ከሁለት ኣመት በፊት በኦሮሞ ክልልና ዘኖች ፣ኣዲስ ኣበባና ኣካቢዋ የነበረ የወጣለት እልቂትም ቢሄር ከቢሄር ግጭት በተለይ ደግሞ ኣመራና ኦሮሞ ትግራይና ኦሮሞ ፣ኦሮሞና ደቡብ ህዝቦች ፣ በነኮንሶና ሌሎች ቢሄረሰቦች ፣ በቤልሸንጎ ጉሙዝና ኣማራ ፣በኣፋርና ኣመራ የነበረም ቢሄር ተኮር መገዳደል ነው ።

በሌላ በኩል የኢህኣደግ ገዥ ፓርት በመላው ሃገራችን የተፈጠረው ትርምስ ኣደገኛ ደረጃ መድረሱና በስብሰባው ውስጥ ያለው ክዳትና ንትርክ እንዳይታወቅ የመንግስት የግል ሚዲያና ማህበራዊ ሚዲያ ፌስቡክ ፣ኢንተርኔት ኣፍኖት በመሰንበቱ ፣ እቺ ኣገር ኣንድነታና ብዙሃንነታ ፣ የዜጎቻ ነጻነት ተጠብቆ እነዳይኖር እያደረጉ ነው የሚገኙ ። ኣሁንም በ11/04 / 2010 ማታ የሰጠው መግለጫም ኣፍ የለለው እንቁላል ኣይነትና የተዳፈነ ነው ።
ከላይ ለተጠቀሰው ችግር ለመፍታት የኢህኣድግና ኣባል ፓርቲዎች በተናጠል ብሄራዊ ፓርቲዎ በሚያደርጉት ግምገማ ይፈታል???

---

ኣሁንስ ቀደምሲል የህወሓት ማ / ኮሚቴ
ስራ ኣስፈጻሚ 5ሳምንት ጊዜ የፈጀ ግምገማ ኣካይዷል፣ የኢህኣደግ ስራ ኣስፈጻሚ ደግሞ በዝግ ቤት ጭንቀት በተሞላበት ግምገማው እያካየደና እየተናጠ ነው ። ሌሎች ፓርቲዎችም ከኢህኣደግ ስብሰባ በኃላ እንደሚገመግሙ ይነገራል ።ለመሁኑ ኢህኣደግ ከነመዋቅሩ የነበረ የመረቱ እና የላሽቁ ኣባላቱ ሰብስቦ ቢናጥ ቢናጥ ለውጢ ያመጣልን ? እስቲ ያለኝን ኣስተያዬት ትንሽ ልበል ፣
1 የህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ስራ ኣስፈጻሚ ለ5 ሳምንታት ያህል ሲገመግም ሰንብቶ በመልካም ኣስተዳደር እንቅፋት የሆኑ ባለስልጣናት ሽምሽር ኣደረግን ፣ማስጠንቀቅያም ሰጥተናል ተብሎ በኣዲሱ ቶሻሚ የህወሓት ሊቀመንበር ለቡዙ ሰኣታት ጊዜ ፈጅቶ ነግሮናል ነግሮናል ። ኣዲሱ ቶሻሚ ደብረጽየን ገብረሚካኤል ግን የነኣባይወልዱ ከሊቀመንበርነት ፣ የበየነ ሞክሩ ከስራ ኣስፈጻሚነት መውረድ እንዲሁም ለሌሎች ማስጠንቀቅያ መሰጠቱ ተነግሮናል ።

በሌላ በኩል የህወሓት ኣማራር ግምገማ በመላው ሃገራችን የሚገኙ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ እስከ ቀበሌ ባለስልጣናት እና ዘመድ ኣዝማዳቸው ፣ራሳቸው ያወጥኟቸው ኣዲስ ስም የተጠመቁ ኮንትሮባንድ ሌቦች የነበሩና ያሉ ፣ እንዲሁም በዘመነ ጠ/ምንስቴር መለስ ኣገዛዝ ኪራይሰብሳቢ የባለስልጣናት ሽሪኮች ሌቦች ፣ ሆዳሞች የሚል ስም የሰጧቸው በሃገራችን ሀብት የቀለዱበት ፣ ኣገር ያጠፉ መሱና ሳይነኩት መውጣታቸው እኒህ መሪዎች ለዚህ ሁሉ ሀብት ወረራ ሰይነኩ የኣባይ ወልዱ የጥቀመኝ ልጥቀምህ ፣ የቤተሰብ ቡዱናውነት እና ኔት

ዎርክ ብቻ ነካክተው ሸውደው መውጣታቸው ለመላው የኢትዮጱያ ህዝቦች በተለይ ደግሞ ከ43 ኣመት በላይ በቅርብ የሚያውቀቸው የትግራይ ክልል ህዝብ እጅጉን አዛዝኖታል።

እንደዚህ ኣይነት በሽወዳ ኣስመስሎ በህዝብ ያለው ኣስተሳሰብ ፤ ተነስተው የነበሩ ጥያቄዎች ፤ ተቃውሞ ለመቀልበስ የበላይ ባለስልጣናት (ቢሌኖሮች ) ነካ ነካ ኣድርጎ በማለፍ በከፍተኛ ባለስልጣናት በተፈጸመውት ገበናዎች ለመታለል በሚዲያዎቻቸው ካስተጋቡ በኃላ ፤ ምንም ወሳኝ ያልሆኑ በዘበኛ ፤በመዝገብ ቤት በተራ ሰራተኛ ፤በቀበሌ ሽሞኞች የነበሩ በመቅጣት ሁኔታው ያበርዱታል ወይ ኣንድ የቀበሌ ወይ የወረዳ ባለስልጣን የማህበረ ሰቡ ሀብት የወረሩ ፤ ህዝብ ያሳቃዩ በኣንድ ቀበሌ እንደዚህ ፈጸመ በማለት ካስተጋቡ በኃላ ወደ ሌላ ወረዳ ወይ ዞን ወይ ከትግራይ ውጭ ወደ ፌደራል ቢሮዎች ይመድቡታል ፤በወረዳ በትንሽ ማንኪያ ከሚበላበት ወደ ፈደራል ወስደው በኣካፋ ወደ እሚበላበት ቦታ ይመድቡታል ። በዚሁ ስልታቸው ህዝብ እያታለሉ ኖሮዋል ። ህዝብ ግን ድሮ ድሮ ነገ ከነገ ወዲያ ይሻሉ ይሆን እያለ ያልፋቸው ነበር ።

በኣሁኑ ጊዜ ግን የኢትዮጱያ ህዝብ ሙሁሩ ፤ተማሪ ፤ ኣርሶ ኣደር ፤ ወዝ ኣደር ፤ ሀቀኛ የሆኑ ባለሀብቶች ነጋዴዎች፤ የራሳቸው ኣባላት ፓርቲ ፤ካድሬዎች ፤ በሀገር ጉዳይ የፓለቲካ ጥያቄ ኣንስተው ግፍ ተፈጽሞባቸው በኣስር ሺህ የሚቆጠሩ የተሳናበቱ በጥሮታ በተለያ ምክንያት በጥሮታ የተሰናበቱ ታጋይ ነበር የጸጥታ ሀይሎች ፤ የመንግስት ስቢል ሰራተኞች ፤ እንዲሁም የሰራተኛ ፤የወጣት ማህበራት ፤ በኢህኣደግ የነበረው እና ያለው እምነቱ ሟጡጦ ጨርሰዋል ። ምክንያቱም ባለፋት 27 ኣመታት ባደራጋቸው ግምገማዎች እና ላመጣቸው ነኝ ያላቸው ለውጦች ሳይፈጽማቸው ቀርቷል (ዋሽቷል) የሚገርመው ግን ኣሁንም ሙሱና ወደጎን በመተው ለውጥ ኣመጣለሁ ማለቱ ኣዲስ የእንለወጥ ኣለን ውሽት እያዬን ነው ።

2 በኣሁኑ ጊዜ እየተካየደ ያለው የኢህኣደግ ማእከላይ ኮሚቴ ስራ ኣስፈጻሚ ግምገማው ስንመለከትም ውጤቱ በህወሓት ማእከላይ ኮሚቴ ስራ ኣስፈጻሚ ከተካየደው ስብሰባ የተለዬ ኣይሆንም ። ምክንያቱም ልዩነቱ የህወሓት ስብሰባ የተካያደው በጠኝ ሰዎችና ነባር ኣማራር በነበሩ ከኣማራሩ የወረዱ ታዛቢዎች ነው ። ተጨማሪ ልዩነት የሚባለው ደግሞ የኣራቱ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው 15 ሰዎች በጠቅላላ 45 ሰወች እና በርከት ያሉ ታዛቢዎችና ተጽኖ ፈጣሪ የሁሉም ነባሮች ማእከላይ ከሚቴ እና የኣጋር ፓርቲ መሪዎች መናሯቸው ነው ። ይህ ኣካየድም ባለፉት 27 ኣመታት እንደሚያካዩዱት የነበረ የጉዛቸው ስልት የሚያመለክት እንጅ በኣመለካከት ይሁን በሀሳብ ኣመንጭነት የተለዬ ለውጥ ሊያመጡ ተብሎ ኣይታሰብም ። በመሆኑም ኣሁንም የሚናገሩትና የሚያዳሙጡት እንደተለመደው ከኣፋቸው ወደ ጀሮ ከጀራቸው ወደ ኣፋቸው ኣዳምጠው መፍትሄ ከመስጠት ውጭ ሌላ የሃገራችን እና ህዝቦቻ መሰረታዊ ሽግሮች ፤ የህክምና መድህኒት ኣግኝተው ውስጣዊ እና ውጫዊ ነባሯዊ ሁኔትቸው የሚፈቱሹበት መንገድ የለም ።

የምናልባች ሊያመጡት የሚችሉ ለውጥ ይኖሯል ብዬ የምገምተው በሃገራችን ያለ ራሳቸው የፈጠሩት ትርምስ የሚፈልጉት የነበረ ሃሳብ ማሳካት ተስኖዋቸው ሁኔታው ሃገራችን ወደ መበታተን ኣቅጣጫ የሚያመራ ሁኔታ እየተፈጠረ ስለሆነ ፤ መላው የኢትዮጱያ ህዝብም በነሱ መተማመን ስላጣ ካሁን በፊት በተለዬ የሚወስዱት እርምጃ ቢኖር ሳይወዱ በግድ በህዝብና ኣለም ኣቀፍ ተጽእኖ ፤ኣሁን ተፈጥሮ ላለው ኣለመረጋት እና የዜጎች እልቂት ለጊዜውም ቢሆን ለመረጋጋት ፤ስልጣናቸው ፤ሀብታቸው በቦታው ለማቆዬት ሲሉ ኣገልጋያቸውና ታማኛቸው የነበሩ በርከት ያሉ መሪዎችና ተከተዮቻቸው ሁኔታው እስከሚረጋጋ ህዝቡ ለማታለል ወይ ኣፍ ኣፍ ለማስያዝ ፤ ከትግራይ ፤ከጎንደር ፤ከጎጃም ዘረኝነት ቀሰቀሳችሁ ዜጎች ኣስጨረሳችሁ ፤የህዝብ የመንግስት ሀብት እንዲወረር እንዲወድም ፤ ዜጎች ከቃያቸው ተፈናቅለው ለስደት እንዲፈናቀሉ ኣድረጋችሁ ተብለው ይታሰሩ ይሆናል ።

ከኦሮሞ መሪዎችም ያፈነገጠ የኦሮሞ ጸጥታ ሀይሎች በሀገራዊ ጸጥታ ሀይሎች ኣፈሙዝ ኣቅንቶ እንዲዋጋ ጦርነት ኣውጃችኃል ዜጎች በጅምላ ኣስገድላችኃል ዘረኝነት ቀስቅሳችሁ ኣገር ወደ ኣደጋ ኣስገብታችኃታል ፣ የመንግስት የህዝብ ሀብት ኣስወርራችኃል ፣ ኣውድማችኃል፣ ከውጭ ጠላቶችና ፣ ጸረህ ገመንግስት ከሆኑ ሃይሎች በመገናኘት የሀገር ክህደት ፈጽሚችኃል እዝብለህዝብ ኣፈጅቷችኃል ፣ ህዝብ ኣፈናቅላችኃል ፣ ለስደት ዳርጋችሁቷል ወ ዘ ተ ተብለው ወደ ወህን ቤትየሚወረወሩእንደሚኖሩ ፣ ክስ የሚመሰረትባቸው ፣ከስልጣን ማስወገድ ሊኖር እና ሽምሽር ሊካሄድ ይችላል ። እስከታች መዋቅርም ወይ ኔትወርክም የህዝብ የጥሏቻ ስሜት ለማብረድ ወይ ለጊዜውም ቢሆንም በወንጀሉ ወሳኝ ያልሆኑ ስህተቶች ይሰሩ ለነበሩ ሰዎች ከስራ ሊባረሩ ይችላሉ ። ይህም ግን ለህዝባችን ኣያረካውም ።ህዝብ የሚፈልገው መሰረታዊ የስርኣት ለውጥ ነው ።

ሌላሊሰሩት የሚችሉ ፈጾሞ የማይሳካላቸው ከሆነ ለነሱ ጥሎ የማይጥላቸው ወታደራዊ ቡዱን ፈጥረው የዙምባቤ ኣይነት መፈንቅለመንግስ ማድረግ ነው ።

ከዚህ ውጭ ግን የኢህኣደግ ማእከላይ ኮሚቴ ስራ ኣስፈጻሚ ቢሆን የህወሓትን ግምገማ ሌጋሲ ተከትሎ እርምጃ ከመውሰድ ውጭ የሙሱና ጉዳይ ኣያነሱም ። ምክንያቱም በሙሱና ቢሌኖሮች እና ሚሌኖሮች የሆኑ ሀገር የወረሩ ፣የንግድ የእንዱስትሪ ፣የባንክ ኢንሽራንስ የኣክስዮን በባለቤትነት የሀገራችን ሀብት በሞኖፓል የያዙ ከነሽሪኮቻቸው ፣ቡዱናቸው በሰንሰለት (በኔት ወርክ ) ኣስፋፍተው የያዙት ከሙቱትና ወደ ወህንቤት (06 ) ካወረዱት የኢህኣደግ ምክርቤት ከጠቅላይ ምንስቴር ቢሮ ፣ሚኒስቴሮች ፣የክልል፣ መሪዎች ኣንባሳደሮች የዞን የወረዳ ቀቤሌ ሌሎችም በሙሉ ወደ ወህን ቤት መውረድ ኣለባቸው ። ይህ ከሆነ ደግሞ ኢህኣደግ በራሱ በሰቀለው ማነቅያ ገመድ ኣይታነቅም ። በመሆኑም የኢህኣደግ ምክርቤት በራሳቸው ሳንባ በሚተነፍሱ ሚዲያዎች በውሼት በተቀናበሩ ኣዋጆችና መግለጫዎቸ ኣማሙቀውን(ሸውደውን ) ሊያልፉ ይሞክሩ ይሆናሉ ።

ይህም የኢትዮጲያ ህዝብ መላው የማህበረሰቡ ክፍሎች መሰረታዊ ለውጥ ሳያዩ ኣይቀበሉትም። ምክንያቱም ህዝቡ በኣሁኑ ጊዜ የመረረውና ችግሩ ያሳቃየው በመሆኑ ከሽግሩ ስለተማረ (ስለነቃ ) ኣይቀበለውም ።

ለዚሁ መሰረታዊ ሽግር መፍትሄ የሚሆን ካሁን በፊት 5 ጊዜ በማህበራዊ መዲያ በጋዜጣ በውጭ ሚዲያዎች የገለጽኩት ቢሆንም ኣሁንም ልድገመው ።

የኢህኣደግ ኣቤታዊ ዲሞክራሲ ኮሚነስት ስነህሳብና ፓሊሲ ወ ዘ ተ ለ27 ኣመት ወይ በዘመኑ ላለው ትወልድ እድሜ ሲለካ ግማሽ ክፍለዘመን መርትዋል ። ህዝብም ዛሬ ነገ ይሻሻላል እያለ ተሸክሞት ኖሮዋል ።ኣሁን ግን እምቢ ኣንፈልጋችሁም ብሎዋችኃል ። ከእንግዲህ ወዲህ ኢህኣደግና የኢትየጲያ ህዝብ ሆድና ጀርባ ሆነናል ብሎዋችኃል። በመሆኑም ኣሁንም ምናልባች ከህዝብ ጋር ያስታርቃችኃል ብዬ ደግሜ እምነግራችሁ !!!

1 ብቻችሁን ቤት ዘግታችሁ ከምተወያዩ በመላው የኢትዮጲያ ህዝቦች በተወከሉ ገለልተኛ ወይ የማንም ፓርት ኣባል ያለሆኑ ወገኖች ኢህኣደግ በገለልተኛና ከፍተኛ ሙሁራን የነበረው ኃላቀር ኣማላካከት ትቶ ሙሁሩ ኣሳትፌ መፍትሄ ያመጣል የሚል እምነት ካለው ባገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ቡቁ ሙሁራን ተመራማሪዎች በተለይ የፖለቲካ ሳይንስ ፣ የህግ የኢኮኖሚ የታሪክ የሌሎች ሙሁራዊ እውቀት ያላቸው ተመራማሪዎች በተለይ ቢሳተፉ ለሰላሙና መረጋጋት ሳይንሳዊ መፍትሄ ሊያገኙ ይችላሉ ።

2 ከሌላ ማህበረሰብ ብቁ እና ገለልተኛ የሆኑ በኢህኣደግ ኣቤታዊ ዲሞክራሲ ኮሚኒስት ኣስተሳሰብ ያልተባላሹ ገለልተኛ የህይማኖት መሪዎች ፣ኣርሶ ኣደሮች ፣ከቡዛህን ማህበራት ፣ የመማህራን ፣የሴቶች ፣የወዝኣደር ፣የሙያ የወጣት ማህበራት ከሁሉም የዩንቨርሲቲ ማህበረሰብ ተወካዮች ፣ የምእራቡም የምስራቁም የኢስያ ፣ የከናዳ ፣የኣውስትራልያ በኣፍሪካ መሪዎች የኣማራር ዘቤ የሚያውቁና በመለው ኣለም የሚገኙ ዲፕሎማቶች ኣንባሳደሮች ተምክሮ ሊያስተላልፉ

የሚችሉ በዲፕሎማሲ ተሰማርተው የበሩ ገለልተኛ ግለሰዎች ፣ ከድሮ ስርኣቶች ወድቀትና እድገት ተሞክሮ ሊያስተላልፉ የሚችሉ ገለልተኛ ቡቁ ባለስልጣናት የነበሩ ከሃገርመከላከያና ሌሎች ጸጥታ ሀይሎች ሂደቱ በመስተካከል ሚና ሊኖራቸው ቡቁ ሰዎች ። የድሮ ኣባት ኣርቦኞች እና ከኢህኣደግ በጥሮታ የተገለሉና ባላቸው ፖለቲካ ኣመለካከት ለኢህኣደግ ኣስተሳሰብና ፖፖሊሲ
ተቃውመው የወጡ
ወ ዘ ተ የተሳተፉበት መሆን ኣለበት ። ኢህኣደግም እንደ ኣንድ ኣካል ሆኖ መክሮ መፍትሄ ቢያመጣ ሁሉም ከተስማሙበት እስከ ህገመንግስት መፈተሽ ቢሄዱ ።

3 በሰላማዊ መንገድ ከኢህኣደግ የተለየ ሀሳብ ይዘው በፓርቲ የተደራጁ የኢህኣደግ ጥገኛ ያልሆኑ ባገር ውስጥና በውጭ ኣገር የሚገኙ ሰላማዊ ፓለቲካ ፓርቲዎች ፣ሌሎች ያገባናል የሚሉ ታዋቂ ፖለቲኮኞችና ታዋቂ ግለሰዎች ።

4 ነፍጥ ኣንስተው የሀገራችን ነጻነት እነራጋግጣለን ባዮች በደፈጣ ውግያ የተሰማሩ በውጭ እና ባገር ውስጥ የሚገኙ ሀይሎች ከሀገራችን የውጭ ጠላቶች መሳሪያነታቸው ኣቁመው ኣገርን ከመውጋት ኣቁመው ለሂወታቸውና ለፓርቲያቸው በኢህኣደግ ዋስትና
ተሰጥቶዋቸው ኣጀንዳቸው ይዘው በሰላምና በእርቅጉበኤ ቢሳተፉ በሰላም ቢሳተፉ ።

4 የግሊሚዲያዎች ነጻነት ኣግኝተው እንዲሳተፉ

5 በዚሁ የእርቂ እና የሰላም ጉባኤ በውሀ ቀጠነ ወህን ቤት ታጉረው ያሉ የፓለቲካ ፓርቲ መሪዎችና የፓርቲ ኣባላት ፣ ጋዜጤኞች ፣የማህበራዊ ሚድያ ጸሀፊዎች በነጻ ተለቀው ሰላሙን በማምጣት ኣስተዋጽኦ እንዲኖሯቸው የሚለው ጥያቄ የሁሉም ኢትየጱያዊ ጥያቄ ነው ።
በመሆኑም ኢህኣደግ ወደደም ጠላም በኣገራችን ያለው ህውከትና ትርምስ ሊፈታ ከሆነ መፍትሄ ይህ ብቻ ነው ። ይህ ኣመለካከት የኣንድ ሁለት ሰው ኣይደለም ።ይህ ኣስተሳሰብ የኢትዮጱያ ህዝብ በሙሉ በዚሁ ኣስተሳሰብ ኣንድ ኣይነት ድምዳሜ ደርሳል ።

ከኣስገደ ገብረስላሴ ፣

መቀለ

15 / 04 / 20 10